# በተለይ ለአማራዎች አንብቡኝ!

## አማርኛችን እንዲዳብር፣አማራነት እንዲጎለብት፣አገርም መልክ እንዲይዝ!

በቅድሚያ ማስታዎስ የምፈልገው እንደአማራ ማሰብ እንድንችል ነው።ሳናስተውል ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚወረወሩልንን ቃላት ወያኔና አነግ ያወጡልንን ሥሞች ጭምር መቀበል ሥለማይገባንና ቀስበቀስ አገር ሸርሻሪና አውዳሚም ሥለሆኑና ሥለማናምንባቸው፣ንቃተ ህሊናችንን በማሳደግ፣

(1ኛ) የአማራ ክልል የሚለውን "የአማራ ክልል ተብዬው" ብለን መናገርና መፃፍ እናዘውትር፣

(2ኛ) የኢትዮጵያ መንግሥት የሚለውን "የትግሬ ወራሪዎች" ፣ የመከላከያ ኃይል የሚለውን "የትግሬ መከላከያ ተብዬው"፣ፌዴራል የሚለውን "የትግሬ ፌዴራል ተብዬው"ወዘተ ብለን መጥራት እንልመድ። ወያኔን አንቀበልም እሥካልን ድረስ እርሱ ያጎረሰንን መዋጥ የለብንም፣ በመሆኑም እሥከዛሬ የምንጠቅምባቸው አነጋገሮች ከእኛ ከአማራዎች ጭንቅላት ተፍቆ መጥፋት አለበት። "**ተብዬው**" የሚለውን ቃል እሥከተጠቀምን ጊዜ ድረስ፣ አለመቀበላችንን ይገልፃል።

(3ኛ) ኢትዮጵያ የኢትዮጵያኖች አገር እንደምንለው፣ኦሮሚ**ያ** ማለት" የኦሮሞ አገር" እንደማለት ነው። "**ያ**" የሚለው ፊደል ተመሳሳይነት ለአገር አመላካችነቱን ግልፅ ያደርገዋል።ይህንንም አነግ ከወያኔ ጋር ሲገዛ ለወደፊት ለመገንጠል እንዲያመቸው አሥቦ ያወጣው እንደሆነ ይታወቅ።ሥለዚህ ከዛሬ ጀምሮ" የኦሮሞ ክልል ተብዬው"፣ "የአፋር ክልል ተብዬው" ወዘተ እያልን ወያኔ እሥኪወገድ ድረስ እንጠቀም። ለአማራው ቆመናል እያልን ተገንጣዮች፣ አገርና ሕዝብ አውዳሚዎች የወረወሩልንን ሥሞች ሳንመረምር እንዳሉ መቀበልና ማስፋፋት ራሳችንን እንደሚያጠፋን እንገንዘብ።

(4ኛ) ከተጀመረ ጀምሮ የፖለቲካ ባህላችን አንድ አሥቀያሚና አንድ ዓይነት የመጠፋፊያ ሥለሆነ እንዲሥተካከል እንጣር፣

(5ኛ) ከዚህ ቀጥሎ አንድ ወንድማዊ አስተያየት ይኖረኛል።ወንድሞቻችን ወንዲራድ አስማማው፣አያሌው መንበርና አቻምየለህ ታምሩ በአንድ ሰብሰባ ላይ ሲወያዩ ልብ ብዬ አዳመጥኳቸው።በንግግራቸውም በጣም ኮርቸባቸዋለሁ። አማራ አማራ ነው፣በርቱልን፣እንበርታ! ጠንክረን ከሰራን ድል ይመጣል፣ከማለት ውጭ የምለው የለኝም።
ውድ ወገኖች! አንድ መሠረታዊ ነገር እንድሠነዝር ፍቀዱልኝ።በአንድ ስብሰባ ላይ የተጠቀማችሁበትን የእንግሊዝኛ ቃላት ልብ እንድትሉት ለግንዛቤ ያህል ከዚህ በታች አሰፍሬዋለሁ።ይህ ለእናንተ ብቻ ሳይሆን እኔም ራሴ፣ራሴን እንድመረምር እረድቶኛል።ሌሎች ወገኖቻችንም ራሳቸውን እንዲመረምሩ ትምህርት ይሰጣል ብዬ አምናለሁ።

ወንድም ወንድይራድ አስማማው!
Geopolitics,expectation,crisis,depression,rubbish,diplomat,lobby,emotion, international community,official,opportunity,below model,external force,British council, Archive center, for sure,financial support.

ወንድም አያሌው መንበር! Challenge,impact, ,from grass root,media,opportunity,challenge,advantage,general view,challenge.

ወንድም አቻምየለህታምሩ!
Animosity,overcome,diaspora,November20,outbreak,challenge,challenge, challenge,challenge,challenge,overcome,overcome,overcome,activism,offlineእናonline,it is natural,universal,reaction,overcome,overcome,an amhara plattform,abandoned.

የእናንተን ሆን ብዬ ተከታትዬ በምሳሌነት ለመጥቀስ ቻልኩ እንጅ፣ከዘጠና አምሥት በመቶ የምንሆነው በውጭ አገር የምንኖረው አማራዎች እንግሊዝኛ ወይም በየምንኖርባቸው ሀገራት የሚገኙትን ቋንቋዎች እንደበላልቃለን።ይህ ለወደፊት መስተካከል ይኖርበታል።
ከአማራው ውጭ ያሉትን በላቲን ፊደላት በሚጠቀሙት የጥቁር ፈረንጆች እየተገረምን እኛው ራሳችን መሰማራታችን አሥደንጋጭ ነው<u>።ለአማራ ሕዝብ የቆምን ሰዎች ለአማርኛ ቋንቋም ዘብ መቆም የግድ ይለናል።</u>

እኛ አማራዎች ሆነን የገዛ ቋንቋችንን ጠላት ሆን ብሎ ሊያጠፋው ሲሯሯጥ በጣም ያሳዝነናል።ሥለዚህ እኛም በምንነጋገርበትና በምንፅፍበት ጊዜ የላቲንን ፊደል ሙሉ በሙሉ አሽቀንጥረን በመጣል በአማርኛ የጀመርነውን በአማርኛ መጨረስ መቻል አለብን፣ ለአማርኛችንም ክብር ከመስጠት አልፎ ያዳብረዋል። እኛንም ያስከብረናል።አለበለዚያ “ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም” ይሆናል። ይህንን አመለካከት ከቅንነት አይታችሁ እንደምትጋሩኝ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ።ይህ ደግሞ የትግላችን “ሀ ሁ” ነው ብዬ አምናለሁ።እናንተም ታውቁታላችሁ፣ግን ሰዎች ነንና ተዘንግቶ ነው ብዬ ነው የምወስደው።

ይህን ካልኩ በኋላ እኛ አማራዎች ቀደም ባሉት ዘመናትም ሆነ ዓመታት በኢትዮጵያ መልክዓ ምድር ሥንኖር የተለያዩትን ነገዶች እንደራሳችን በመቁጠር ጠንካራ አንድነት ያለን መሥሎን ተዘናግተን ኖረናል።
ነገር ግን ከ25ዓመት ወዲህ በወያኔ፣በኦነግ፣በኢሥላማዊ የኦሮሞ ድርጅት፣በኦህዴድ፣በደቡብ በእነሽፈራው ሽጉጤ፣በመተከል፣በአፋር፣በኦጋዴን፣ወዘተ አማራ በአማራነቱ ተለይቶ ሲባረር፣ ሲፈናቀል፣ ሲደበደብ፣ ሲታሰርና ሲገደል በአጠቃላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈፀምበት መስማትና ማዬት የተለመደ ዜና ሆኖ ቆይቷል።

በ1984ዓም የመላ ዐማራ ሕዝብ ድርጅት(መዐሕድ)በክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ መሪነት ተቋቁሞ ባደረገው ጥረት፣ በአራት እግሩ መሄድ የጀመረውን ዐማራ ቀና ብሎ በሁለት እግሩ እንዲሄድ ለማድረግ ጣረ። ነገር ግን ወያኔ የእንቅስቃሴውን እየጠነከረ መሄድ ባጤነ ጊዜ ፕሮፌሰርንና ብዙ ጠንካራ አማራዎችን ገደለ።እንደ ድርጅት መሪዎቹ ሲያዙና ሲጠፉ ተከታዮቹ ብቅ ብለው በመታገል ቀጣይነት ያለው ሥራ መሥራት ይጠበቅ ነበር።የሆነው ግን ተቃራኒው ነው። ምክንያቱም የእኛ የተከታዮቻቸው ንቃተ ህሊና ዝቅተኛ በመሆኑ እርስ በእርስ በመፍረክረክ መለያየትን መረጥን። ድርጅቱም ተዳከመ።በመጨረሻም ወደመኢአድ ተቀይሮ ቅንጅትን ከፈጠሩት ድርጅቶች ግዙፉ እንደነበር አይካድም። ምንም እንኳን ቦርቧሪዎቹ ቢበዙም፣ከቅንጅት መፍረስ በኋላም ወደመኢአድ ተመልሶ የቻለውን ያህል ጥረት ሲያደርግ ተስተውሏል።

እንደሚታወቀው ዛሬ ወያኔ ሲገባ ወጣቶች የነበሩና ወያኔ ከገባ በኋላ የተወለዱ አማራዎች ሸክሙ ከሚችሉት በላይ ሥለሆነባቸው፣በመኖርና ባለመኖር አጣብቂኝ ውስጥ በመውደቃቸው "በግዳጅ ትግሬ ሁኑ አትበሉን፣አማራ ነን፣ማንነታችንን አትንጠቁን" በማለት ለአማራ ማንነትና ህልውና መቆም ግድ አላቸው ።በመሆኑም ከዘረኞቹ ትግሬዎች ጋር ግብግብ ገጠሙ።ሳይውል ሳያድርም በመንግሥት ተብዬዎቹ ትግሬዎች የጦርነት አዋጅ ተበይኖባቸው፣የአማራን ዘር ለማጥፋት ሌት ተቀን እየተሰራበት ይገኛል።

ዛሬ አማራ በአማራነቱ የአማራን ህልውናና ማንነት ለማስመለስና ለማስከበር ከወያኔ ጋር ግብ ግብ መግጠሙ ያሥደነገጣቸው እነብርሀኑ ነጋ "ላሊበላ በሰው ሠርግ ይዳራል እንዲሉ"ሳይዋጉ ድልን መጎናፀፍ ሥላማራቸው፣የአማራውን ትግል የእኛ ነው እሥከማለት ደርሰዋል። ፀረ-አማራው ብርሀኑ ነጋ የአማራውን ነፍሰ ገዳይ ሌንጮን እየጎተተ ላይ ታች እያለ የአማራውን ትግል ለማዳከም ሲጥር ይሥተዋላል። ብርሀኑ ከሌንጮ ጋር ፈጠርኩት የሚለው የማጭበርበሪያ ድርጅት የእርሱንና የሦሥት የዘር ድርጅቶችን የያዘ የ<u>ኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ</u> የሚል ነው ።
የአማራው ብሔር ለምን በዚህ ሥብስብ ውስጥ አልተወከለም ተብሎ ብርሀኑ ሲጠየቅ፣ የተሰበሰበውን ሕዝብ ከመናቁ የተነሳ ብሔርና ድርጅት የሚሉትን የማምታቻና የመዋሻ ቃላቶች በመደርደር ተሰብሳቢውን ለማሳመን ጥሯል። ምናዓይነት ተሰብሳቢ ነው እየተሰደበ የሚያጨበጭብ።
(1ኛ) አንባቢ! ያሰመርኩባቸውን ብቻ ደጋግሞ ያንብበው።

"የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ <u>የብሔሮች ሥብስብ አይደለም።</u>
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ <u>የድርጅቶች ሥብስብ ነው</u>(ጭብጨባው ቀለጠ)
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ <u>በብሔር የተደራጁ አሉበት</u>፣በሕብረ ብሔር የተደራጁ አሉበት"።

የብሔር ሥብስቦችን አቅፎ ሀገራዊ ንቅናቄው የብሄሮች ሥብስብ አይደለም ብሎን አረፈ፣ሌላኛው ሽወዳ ደግሞ የድርጅቶች ስብሰብ ነው የሚለው ነው።

በነገራችን ላይ አጨብጫቢዎቹ ተገዝተው ነው፣ወይም ፍሬ ነገሩ ገብቷቸው ነው እንዳልል፣ አልገባቸውም። ለነገሩማ አንዱ ለንደንስ ላይ ኢትዮጵያ ፈርሳ ኦረሚያ ትገነባለች ሲል ጭብጭባ ቀልጦ የለም። ጉድ ነው ዘመናችን።

ምንም እንኳን ለማንም ተራ ሰው ቁልጭ ያለ ሀቅ ቢሆንም ቅሉ፣አንባቢ ልብ ብለህ ተከታተለኝ።

የሴቶች ማህበር(ድርጅት)፣የወጣቶች ማህበር(ድርጅት)፣የብሄር ንቅናቄ(ድርጅት)፣የህብረብሄር ፓርቲ (ድርጅት)፣ግንቦት ሰባት(ድርጅት)፣አሁን እነብርሀኑ ፈጠርነው የሚሉት ሀገራዊ ንቅናቄ(ድርጅት)፣የሌንጮ የኦሮሞ ግንባር ብሔር(ድርጅት)፣የአፋር ብሔር(ድርጅት)፣ የሲዳማ ብሔር(ድርጅት)፣ቤተ አማራ ብሔር(ድርጅት)፣ዳግማዊ መ ዕሕድ የአማራ ብሔር(ድርጅት)፣ሞረሽ የአማራ ብሔር(ድርጅት) የአማራ ሕዝብ መድህን ንቅናቄ(ድርጅት) ወዘተ የሁሉም አጠቃላይ ስማቸው ድርጅት ነው።

ብርሀኑ ግን በተፈጥሮው ዘረጦና ውሸት ቋቱ ሥለሆነና ያን ከጥንት ተያይዞ የመጣውን የአማራ ጥላቻ እንደተሸከመ በግልፅና በማያሻማ ቋንቋ እንዲህ ብሎናል።

"የአማራውን ድርጅቶች **የብሔር ሥለሆኑ** ድርጅቶች አይደሉም፣ ከእኛም ጋር አልተካተቱም። የሌንጮየአፋርየሲዳማድርጅቶች **የብሔር ቢሆኑም** ድርጅቶች ናቸው፣ከእኛም ጋር ሊካተቱ በቅተዋል" በማለት በድፍረት ነግሮናል።
ሁለተኛ ብርሀኑ ቆዳውን ሲያዋድድ እንዲህ ብሏል። "3 እና 4 እየሆኑ ብሔር እንወክላለን ይላሉ።ከ እኛ ጋር ካልሰሩ አይሆንም እንዴ" ሲልና ቱልትላውን ሲነፋ ተደምጧል።

**(2ኛ)** ብርሀኑ!በመጀመሪያ 3 እና 4 ስላለው
ብርሀኑእዋጋለሁ ብሎ ከዋሸበት ቀንና ዕለት ጀምሮ እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ፣ግራ የገባቸውን የተወሰኑ የመሀል አገር ሰዎችን፣ሰባት ቤት ጉራጌን ከምባታን ቢሰባስብም ቁጥሩ አልባሌ ሆነበት። በአባይም ሆነ በክርሥትና ሀይማኖት ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ ታሪካዊ ጠላትነት ካላቸው ሀገራት ገንዘብ እያግበሰበሰ ኢሳትንም በቁጥጥሩ ሥር አውሎ፣አልፎ ተርፎ ለሥራ ፈቶች ተዳርሶ፣እነኚህ ሥራ ፈቶች በየቦታው ተሰማርተው "ውሻ በበላበት ይጮህል" እንዲሉ፣ የአማራውን ታጋዮች ሲሳደቡ ይውላሉ።
ለሆዳቸው ያደሩና ለሥልጣን የቋመጡ ጥቂት ያልዘሩ በቀል እንደሞላ ዓይነት አማራዎችን ቢገዛም የአማራን ትግል ከሚደግፈው ጋር ሲወዳደር ብርሀኑ አጫፋሪዎች ካልሆኑ በስተቀር የሚፎልለውን ያህል አባላት እንደሌለው ተረድቶታል።ታዲያ" ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" እንዲሉ፣ዕውነታው ይህ ሆኖ ሳለ 3እና 4 ሆነው የሚለው የዋሾው አነጋገር ማንን ለማሳመን ነው።

**(3ኛ)** የብርሀኑ ሌላኛው መመጻደቂያ ሆኖ የቀረበው ከእኛ "የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ"ጋር ካልሰሩ አይሆንም እንዴ"! የሚል ነው።
በመጀመሪያ በዚህ "መልከ ጥፉ በሥም ይደግፉ" በሆነ ንቅናቄ ተብዬው አማራው እንኳን ሊካፈል ሲያልፍም አይነካውም።

ለማንኛውም አማራ ነኝ ለሚል ወገን እንዲረዳልን የምንፈልገው ከዚህ የሚከተለውን ነው።

| |
|---|
| አማራው አሁን ያለበት ሁኔታ ከ25ዓመት በላይ የዘር ማጥፋት ሲደረግበት፣ ሲቀጠቀጥና ሲገደል ሲሳደድ፣ርስቱን፣ሚስቱን፣ልጁን ሲቀማ ኖሮ የተረፈውም በመንግሥት ተብዬው በአዋጅ የትግሬ ዘረኛ ወራሪዎች ጦርነት ታውጆበት ዘሩን ከጥፋት ለመታደግ ከወያኔ ጋር ግብግብ ገጥሞ ሲዋደቅ እያየን ነው።ሥለዚህ የአማራው ትግል በመኖርና ባለመኖር መካከል አጣብቂኝ ውስጥ ሥለሚገኝ፣ የህልውናና **የአማራ ማንነት ጥያቄ ነው። ዛሬ አማራው ለአማራ ማንነትና ለህልውናው መቆም ባልቻለበት ወቅት፣በቅንጅት ጊዜ እንዳደረገው ለኢትዮጵያ አንድነትም ሆነ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲቆም ግፊት ማድረግ ቀሪው አማራ ከምድረገፅ እንዲጠፋ ከሚመኙ ጠላቶች የሚመነጭ ነው።** የአማራውን ጉዳትና ብሶት እንጋራለን፣አማራው በሁለት እግሩ ካልቆመ ኢትዮጵያም አትቆምም፣ አንድነትም ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትም አይታሰብም የሚሉ ወዳጆቻችን ናቸው።ይህንን አንጋራም ያሉም አይነካኩን አርፈው ይቀመጡ፣ካልተቀመጡና ከተሞጣሞጡ "በሰው ቁሥል እንጨት ሥደድበት" እንደሆነ ተረድተን አሥፈላጊውን ከመውሰድ ወደኋላ አንልም።ለእኛ አማራነት በመወለድ ብቻ ሳይሆን ለአማራ በመሥራትም እንደሆነ እንዲታወቅ።በተለይ አማራ ያልሆኑ ጣልቃ ገብተው ሊፈተፍቱ ከቶውንም አንፈቅድላቸውም ምክንያቱም አያገባቸውምና። |

የብርሀኑ ግንቦት፣የጎንደር ህብረት፣የጎጃም፣የወሎ የሸዋ፣የጂኒጃንካ የአማራን ማንነት ለመቀልበስ ከየአቅጣጫው ያሰፈሰፉ ግልባጭ ወያኔዎች ብቅ ብለው ደንቃራ መሆን ጀምረዋል።

ሥለዚህ ከእንግዲህ ብርሀኑ ፀረ-አማራና ዋሾ መሆኑን ካረጋገጥን እሥከመጨረሻው ትግላችንን እንድንገፋ አደራ እላለሁ።

በመጨረሻም ለእህታችን ርስቴ ተስፋዬ፣ለወንድሞቻችን ለሄኖክ የሺጥላ፣ለዶክተር አቤል፣ለአንተነህ ሙሉጌታ ወዘተ የምለው አለኝ። ጠላታችን ወያኔ ብቻ ሳይሆን  ፀረ-አማራ የሆኑ ከብርሀኑ ግንቦት 7 ጭምር   ያሉ ኃይላት እንደሆኑ እናውቃለን።እነኚህ ጠላቶች እንዳበደ ውሻ ሲቅነዘነዙ ማዬት ያስደስታል።እናንተ በድፍረት ወጥታችሁ እነዚህን ኃይላት ሥለምትታገሏቸው ሲንጫጩ ይደመጣሉ። ለወገናችን አመርቂ ሥራ ሥለምትሰሩ በየጊዜው ጠላቶች ሥማችሁን ያነሱታል። ይህ የሚያኮራችሁ እንጅ የሚያሸማቅቃችሁ እንዳልሆነ ተገንዝበናል።እኛም ከጎናችሁ ነን። በርቱ እንበርታ። ለዚህ ጠላት ለበዛበት ሕዝብ ድምፅ በመሆናችሁ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ።በርቱ፣ እንበርታ።

ኃይሉ በላይ